የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

**(ግንቦት 20- 26/2016 ዓ.ም)**
May 27- June 3/2024

## በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ

**1. የኮንስትራክሽን ጥሬ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ሊዘጋጅ ነው**

መንግሥት የኮንስትራክሽን ዘርፉን ለመደገፍ ከውጭ የሚገቡ ጥሬ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ሊያዘጋጅ መሆኑን፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ ተናገሩ፡፡

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህንን የተናገሩት ‹‹ቢግ 5 ኮንስትራክት ኢትዮጵያ›› የተሰኘ ድርጅት፣ ከግንቦት 22 እስከ 24 ቀን 2016 ዓ.ም. የሚቆይ ዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዓውደ ርዕይና ሲምፖዚየም ላይ ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር ሲያደርጉ ነው፡፡

***ሪፖርተር June 2, 2024***

‹‹ኢትዮጵያን እንገንባ!›› በሚል መሪ ቃል በተካሄደው ዓውደ ርዕይ ላይ ንግግር ያደረጉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በኮንስትራክሽን ኢንቨስትመንት ዘርፍ የተሰማሩ ተቋማት ምቹ ምኅዳር ለመፍጠር ዝግጅት እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ፈጠራን በማጎልበት የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሞተር መሆኑንና በአገር ውስጥ ያለው ጥቅል ምርት 21 በመቶ ድርሻ መያዙን የገለጹት አቶ ተመስገን፣በ2014 ዓ.ም. ዘርፉ የሚያንቀሳቅሰው 54.8 ቢሊዮን ዶላር እንደነበር አስረድተዋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/130035/

**2. የኢትዮጵያ እና ኮሪያ ሪፐብሊክ የተፈራረሙት የፋይናንስ ልማት ትብብር ስምምነት የአገራቱን የኢኮኖሚ ትስስር ይበልጥ የሚያጠናክር ነው**

የኢትዮጵያ እና ኮሪያ ሪፐብሊክ የተፈራረሙት የፋይናንስ ልማት ትብብር ስምምነት የአገራቱን የኢኮኖሚ ትስስር ይበልጥ የሚያጠናክር መሆኑን የገንዘብ ሚኒስትሩ አህመድ ሽዴ ገለጹ።

**ኢዜአ ግንቦት 25/2016**

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው ለይፋዊ የሥራ ጉብኝት ኮሪያ ሪፐብሊክ ሴኡል ገብተዋል።

በዛሬው እለትም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከኮሪያው ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት ዩን ሱክ ይኦል ጋር የሁለትዮሽ ውይይት አድርገዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_4530463

**3. የውጭ አገር ህጋዊ የሥራ ስምሪትን ከመካከለኛው ምስራቅ በተጨማሪ ወደ አውሮፓና ኤስያ ለማስፋት እየተሰራ ነው - ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚል**

የውጭ አገራት የስራ ስምሪትን በሚመለከት ከኢዜአ ጋር ቆይታ ያደረጉት የሥራና ክህሎት ሚኒስትሯ ሙፈሪሃት ካሚል፤ከአገራት ጋር ህጋዊ የሥራ ስምሪት ስምምነት በማድረግ የሰለጠነ የሰው ሃይል ስምሪት እየተሰጠ መሆኑን ገልጸዋል።

**ኢዜአ ግንቦት 25/2016**

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_4528692

**4. ለህዳሴ ግድቡ ግንባታ ከወጣው 192 ቢሊዮን ብር ውስጥ 95 በመቶው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብድር መሸፈኑ ተገለጸ**

ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ እስካሁን ከተደረገው ጠቅላላ ወጪ ውስጥ ከ95 በመቶ በላይ የሚሆነው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተገኘ ብድርና ድጋፎች የተሸፈነ መሆኑ ተገለጸ። ባንኩ ለግድቡ ግንባታ ከሰጠው ብድር በተጨማሪ በብድሩ ላይ ማስከፈል የነበረበትን የወለድ መጠን በእጅጉ ዝቅ በማድረግ በየዓመቱ ሊያገኝ የሚችለውን ከ15 ቢሊዮን ብር በላይ የወለድ ገቢ ማስቀረቱም ታውቋል።

***ሪፖርተር June 2, 2024***

ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ማጠናቀቂያ የሚውል የገንዘብ ድጋፍ በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን (የኢትዮጵያ ዲያስፖራ) ለማሰባሰብ የሚያስችል አዲስ መተግበሪያ በተጠናቀቀው ሳምንት ይፋ በተደረገበት ፕሮግራም ላይ እንደተገለጸው የግድቡ ግንባታ ከተጀመረበት ወቅት አንስቶ እስከ የካቲት 2016 ዓ.ም. (ማለትም ላለፉት 13 ዓመታት) ድረስ ለግድቡ ግንባታ 192 ቢሊዮን ብር ወጪ ተደርጓል፡፡

**5. የንግድና መረጃ ማዕከል ለመፍጠር የተጀመረው የኢንዱስትሪዎች ቆጠራ በመስከረም ወር እንደሚጠናቀቅ ተነገረ**

በአገር አቀፍ ደረጃ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ያሉ የኢንዱስትሪ ተቋማት፣ የራሳቸው የንግድ መረጃ ማዕከል ኖሯቸው በምርትና በግብዓት ትስስር እንዲፈጥሩ ለማድረግ የተጀመረው ቆጠራ፣ በመስከረም ወር 2017 ዓ.ም. እንደሚጠናቀቅ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

***ሪፖርተር June 2, 2024***

የኢንዱስትሪዎች ቆጠራ በኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት አማካይነት እየተደረገ መሆኑንና በ2016 ዓ.ም. ሚያዝያ ወር ውስጥ ለሙከራ ያህል በደብረ ብርሃን፣ በወላይታ ሶዶ፣ በአምቦና በአዳማ አካባቢዎች ቆጠራ መካሄዱን፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጥላሁን ዓባይ ለሪፖርተር ተናግረዋል፡፡

**https://www.ethiopianreporter.com/130031/**

**6. አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ተግባራዊ መደረጉ በአፍሪካ ሁሉን አቀፍ እድገት እንዲኖር እንደሚያደርግ ተገለጸ**

የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና (ኤ ኤፍ ሲ ኤፍ ቲ ኤ) ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ መደረጉ በአህጉሪቱ ሁሉን ያሳተፈ ዕድገት እንዲኖር እንደሚያደርግ የአፍሪካ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ተናግረዋል።

**Fana ግንቦት 20፣ 2016**

በኬንያ ናይሮቢ በተካሄደው 59ኛው የአፍሪካ ልማት ባንክ የገዢዎች ቦርድ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ፥ አህጉራዊ የንግድ ልውውጥ ሲጨምር አፍሪካ በምዕራባውያን ገበያ ላይ ያላት ጥገኛነት እንደሚቀንስ ተጠቁሟል።

የአፍሪካ ልማት ባንክ ቡድን ዋና ጸሃፊ ቪንሰንት ንመሂሌ በዚህ ወቅት ፥ በአህጉሪቱ በሚመረቱ ሸቀጦች ላይ የገቢ ቀረጥ በማስቀረት በመላው አፍሪካ ያለውን የንግድ ልውውጥ ነፃ ማድረግ የአፍሪካን የንግድ ልውውጥ ያሳድጋል ፤ አነስተኛ የንግድ ተቋማትንም ተጠቃሚ ያደርጋል ብለዋል።

https://www.fanabc.com/archives/247724

## 7. ኢትዮጵያ ዕምቅ የማዕድን ሃብት ስላላት በዘርፉ ለመሠማራትና ትስስር ለመፍጠር እንሠራለን ሲሉ የፓኪስታን የንግድና የኢንቨስትመንት ልዑክ አባላት ገለጹ፡፡

የማዕድን ሚኒስትር ሀብታሙ ተገኝ (ኢ/ር) እና የፓኪስታን የንግድና የኢንቨስትመንት ልዑክ አባላት በአዲስ አበባ ተወያይተዋል፡፡

**Fana ግንቦት 20፣ 2016**

በዚሁ ወቅትም ለልዑካን ቡድኑ አባላት በማዕድን ዘርፉ ያሉ የኢንቨስትመንት አማራጮች ገለጻ የጠደረገ ሲሆን፥ በዘርፉ እንዲሰማሩ ጥሪ መቅረቡንም የሚኒስቴሩ መረጃ አመላክቷል፡፡

https://www.fanabc.com/archives/247821

## 8. በኢትዮጵያ 200 የታዳሽ ኃይል ፕሮጀክቶች እየለሙ ነው

በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የሚኒስትሩ ከፍተኛ የኢነርጂ አማካሪ አቶ ጎሳዬ መንግስቴ በሀገሪቱ እየተካሄዱ ያሉትን የታዳሽ ኃይል ፕሮጀክቶች አስመልክተው እንደተናገሩት፤ መንግሥት በታዳሽ ኃይል ዘርፍ የኅብረተሰቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚያሻሽሉ ፕሮጀክቶችን ለማስፋፋት ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት ላይ ነው፡፡

**Ethiopia press agency June 3, 2024**

ባለፉት ዓመታትም 11 የታዳሽ ኃይል ፕሮጀክቶች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በሙከራ ደረጃ ሲከናወኑ መቆየታቸው አስታውሰው፤ በአሁኑ ወቅት በመካሄድ ላይ ያሉት ፕሮጀክቶች ቁጥሩን ወደ 200 ያደርሱታል ብለዋል፡፡ ይህም ዋናው የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት በማይደርስባቸው አካባቢዎች ለሚገኙ ነዋሪዎች አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

https://press.et/?p=129125

# በውጭ ቋንቋዎችና ከውጭ ሚዲያዎች

## 9. Digital modernization key to avoiding EU ban on Ethiopian flowers

Ethiopia's horticulture sector, particularly its flower industry, faces a significant challenge as a potential European Union (EU) ban looms due to quality issues. The sector must modernize digitally to address these problems and maintain its major market destination.

**Capital Ethiopia May 27, 2024**

The National Bank of Ethiopia (NBE) reported that Ethiopia's cut flower exports generated nearly $600 million in revenue for the 2022/23 fiscal year, making it the second-highest-valued export product after coffee. More than 85% of these cut flowers are exported to Europe, and floriculture accounts for 8% of the country's export revenue. Despite this impressive growth, quality issues on some farms continue to affect the industry.

https://www.capitalethiopia.com/2024/05/27/digital-modernization-key-to-avoiding-eu-ban-on-ethiopian-flowers/

## 10. Blueprint for global financial architecture that works for Africa

African leaders have finally laid out the blueprint for the financial architecture that many of the continent's political bigwigs and economists have been calling for, clearly painting the picture that has been at best a silhouette in recent years.

**THE EAST AFRICAN JUNE 02 2024**

Over the past two years, leaders on the continent, as well as civil societies and economic think tanks, have raised concerns over how the international financial architecture is designed, saying it does not work for Africa.

https://www.theeastafrican.co.ke/tea/business/blueprint-for-global-financial-architecture-for-africa-4643442

## 11. Nairobi Kenya hosted the 59th Annual Meetings of the African Development Bank (AFDB).

Over 3,000 participants from 82 countries attended the 5-day event.

A Reform of the Global Financial Architecture to take into account climate-related challenges was high on the agenda this year.

**African news May 31, 2024**

The Afdb says that African countries should mobilize 213 billion dollars annually from the private sector to bridge the climate financing gap by 2030. This is a priority for the bank's outgoing president.

https://www.africanews.com/2024/05/31/afdbs-annual-meetings-end-in-nairobi/

## 12. EU agrees tariffs on Russian, Belarusian grain imports from July

European Union trade ministers have agreed to impose prohibitive tariffs on grain and other agricultural products from Russia and Belarus from July 1.

**Aljazeera May 30, 2024**

The tariffs will be 95 euros ($102.76) per tonne for cereals and 50 percent of their value for oilseeds. Tariffs will also apply to beet-pulp pellets and dried peas. The ministers' decision on Thursday follows a proposal from the European Commission on March 22.

The announcement of the new tariffs quickly drew Russian disapproval.

**https://www.aljazeera.com/economy/2024/5/30/eu-agrees-tariffs-on-russian-belarusian-grain-imports-from-july**